# የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት
# የኤሌክትሮኒክ ትምህርት ማስተግበሪያ
# መመሪያ ቁጥር 1044/2017

## መመሪያ ቁጥር፡ 1044/2017

የካቲት 2017 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## መግቢያ

መንግስት ዜጎች ጥራት እና ተገቢነት ያለው ትምህርትን ፍትሃዊ በሆነ መንገድ እንዲያገኙ ለማድረግ አሁን እየተሰጠ ባለው የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ በተጨማሪ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በኤሌክትሮኒክ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ ትምህርትን መስጠት አስፈላጊ በመሆኑ፣

ዜጎች በተለያየ ምክንያት ማግኘት የማይችሉትን ትምህርት እንዲያገኙ በማድረግ የትምህርትን ተደራሽነትን፣ ተገቢነትና ጥራት፣ ፍትሃዊነትን ለማረጋገጥ እና የዜጎችን የመማር ዕድል ለማሳደግ የሚያስችል ወሳኝ መሳሪያ መሆኑ ስለታመነበት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ትምህርት ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 1152 /2011 ዓ.ም አንቀጽ 95 (2) እና አንቀጽ 18 (2) መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**1. አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "**የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የኤሌክትሮኒክ ትምህርት ማስተግበሪያ መመሪያ ቁጥር** 1044/2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**2. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ፡-

1. "**የኤሌክትሮኒክ ትምህርት**" ማለት የመረጃ እና መገናኛ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ሙሉ በሙሉ በበይነመረብ እና በተቀናጀ ዘዴ የሚሰጥ ትምህርት ነው።
2. "**የመስመር ላይ ትምህርት**" ማለት መምህሩ እና ተማሪው በአካል ሳይገናኙ በበይነ መረብ አማካይነት የሚሰጥ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ ነው፡፡
3. "**የመስመር ላይ ትምህርት መድረክ**" ማለት በይነ መረብን በመጠቀም የኤሌክትሮኒክ ትምህርት ለመስጠት የሚያገለግሉ የተለያዩ ማስተግበሪያዎችን አቀናጅቶ የሚይዝ ቴክኖሎጂ ነው፡፡
4. "**የመረጃ ደህንነት**" ማለት በኤሌክትሮኒክ ትምህርት አሰጣጥ ስርዓት ውስጥ የሚሳተፉትን ግላዊ እና ተቋማዊ መረጃዎችን ላልተፈቀደለት አካል እንዳይደርስ እና ላልተፈቀደለት ዓላማ እንዳይውል መከላከል ነው።
5. "**የኤሌክትሮኒክ ትምህርት ኮሚሽን**" ማለት በአንድ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ከተለያዩ የስራ ክፍሎች የተውጣጡ አባላትን ያቀፈ በኤሌክትሮኒክ ትምህርት አተገባበር ላይ ውሳኔዎችን እና አቅጣጫዎችን የሚያስቀምጥ አካል ነው፡፡
6. "**የኤሌክትሮኒክ ትምህርት አስተዳደር ዳይሬክተር**" ማለት በከፍተኛ ትምህርት ተቋም ደረጃ የኤሌክትሮኒክ ትምህርትን በኃላፊነት የሚመራ ኃላፊ ነው፡፡
7. "**የኤሌክትሮኒክ ትምህርት አስተባባሪ**" ማለት በከፍተኛ ትምህርት ተቋም በኮሌጅ ወይም በትቋም ወይም በፋክልቲ ደረጃ የኤሌክትሮኒክ ትምህርትን በባለቤትነት የሚያስተባብር ነው፡፡
8. "**የትምህርት አይነት**" ማለት በመንፈቀ ዓመት ጊዜ ውስጥ የሚሰጥ የተደራጀ ትምህርት ነው።
9. "**የኤሌክትሮኒክ ትምህርት ይዘት**" ማለት የኤሌክትሮኒክ ትምህርትን እውቀት፣ ክህሎት እና አመለካከት በአጠቃላይ ብቃትን ሊያስጨብጥ የሚችል በጽሑፍ፣

በተንቀሳቃሽ ምስል፣ በድምጽ፣ በሥዕልና በመሳሰሉት የሚቀርብ የትምህርት አይነት ይዘት ነው፡፡

10. **“መልቲ ሚዲያ ስቱዲዮ”** ማለት የኤልክትሮኒክ ትምህርት የትምህርት አይነት ይዘት በምስል፣ **በድምጽ፣ በምስለ ድምጽ** እና በጽሑፍ የሚዘጋጅበት እና የሚደራጅበት ማዕከል ነው።

11. “**የትምህርት ፕሮግራም**” ማለት የተቀናጁ የትምህርት ዓላማዎችን ለማሳካት የተነደፉ እና የተደራጁ የትምህርት ተግባራት ስብስብ ወይም ቅደም ተከተል ወይም የተወሰኑ የትምህርት ተግባራትን በዘላቂ ጊዜ ውስጥ ማከናወን ነው።

12. “**የትምህርት አይነት**” ማለት በመንፈቀ ዓመት ጊዜ ውስጥ የሚሰጥ የተደራጀ ትምህርት ነው።

13. በዚህ መመሪያ በወንድ ፆታ የተገለፀው አነጋገር የሴትንም ይጨምራል፡፡

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ለትምህርት ሚኒስቴር ተጠሪ በሆኑ ሁሉም የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 4. የመመሪያው ዓላማ

በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተለያዩ የማስተማሪያ የመስመር ላይ ትምህርት መድረኮችን በመፍጠር እና ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ግልጽ እና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ የትምህርት ተደራሽነትን፣ ፍትሃዊነትን፣ ጥራትና ተገቢነትን በማረጋገጥ ትምህርትን ለሀገር ልማት ማዋል ነው፡፡

## 5. መርህ

ሁሉም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በኤሌክትሮኒክ የሚሰጠውን ትምህርት ተደራሽነት፣ ጥራት፣ ተገቢነት፣ ፍትሃዊነት፣ ወጪ ቆጣቢነት እና ውጤታማነት በሚሻሻልበት መርህ ላይ የተመሰረቶ የሚተገበር ይሆናል።

## ክፍል ሁለት

## የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የኤሌክትሮኒክ ትምህርት ፕሮግራም ተቋማዊ አደረጃጃት

### 6. የከፍተኛ ትምህርት የኤሌክትሮኒክ ትምህርት መዋቅራዊ አደረጃጃት

በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚኖረው የኤሌክትሮኒክ ትምህርት መዋቅራዊ አደረጃጀት እንደሚከተለው ይሆናል።

1. የኤሌክትሮኒክ ትምህርት አስተዳዳር ዳይሬክቶሬት፣
2. የኤሌክትሮኒክ ትምህርት ኮሚሽን፣
3. የዩኒቨርሲቲው ሬጅስትራር ጽ/ቤት፣
4. የትምህርት ጥራት ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት፣
5. ኮሌጅ  ወይም ተቋም ወይም ፋክልቲ፣
6. የመረጃና ግንኙነት ቴክኖሎጂ ክፍል፣
7. የተከታታይ እና ርቀት ትምህርት ክፍል፣
8. አብያተ- መጻህፍት፣ እና
9.  የኮሌጅ ኤሌክትሮኒክ ትምህርት ማስተባበሪያ፡፡

### 7. የኤሌክትሮኒክ ትምህርት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

የኤሌክትሮኒክ ትምህርት አስተዳደር ክፍል የሚከተሉት የተለያዩ ግብዓቶች እና የሰው ኃይል አደረጃጀት ይኖሩታል።

1. የኤሌክትሮኒክ ትምህርት አስተዳደር ክፍል እንደ ተቋማቱ መዋቅራዊ ሁኔታ ተጠሪነቱ ለአካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዝዳንት ወይም የአካዳሚክ፣ የምርምር፣ የቴክኖሎጂ ሽግግርና ማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዝዳንት ሆኖ የራሱ ዳይሬክተር፣ ተገቢው ቢሮና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ይኖረዋል፡፡
2. እንደተቋሙ ሁኔታ እና አቅም እየታየ በርካታ ኮሌጆች ያሉት ወይም ከበርካታ ኮሌጆች ጋር የሚገናኝ ከሆነ በየኮሌጁ የኤሌክትሮኒክ ትምህርት አስተባባሪ እንዲኖራቸው ይደረጋል።

3. የኤሌክትሮኒክ ትምህርት አስተዳደር ክፍል ከሁሉም ትምህርት ክፍሎች ጋር በተቀናጀ ሁኔታ ስራውን ያከናውናል፡፡

## 8. የኤሌክትሮኒክ ትምህርት ኮሚሽን

1. ኮሚሽኑ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል።

ሀ. የኤሌክትሮኒክስ ትምህርት አስተዳደር ዳይሬክተር የኮሚሽኑ ሰብሳቢ ሆኖ፤

ለ. በኮሌጆች ወይም በተቋሞች ወይም በፋኩልቲዎች አንዳንድ አስተባባሪዎች፤

ሐ. የመረጃና ግንኙነቶች ቴክኖሎጂ ክፍል ኃላፊ፤

መ.የትምህርት ጥራት ማሻሻያ ክፍል ኃላፊ ፤

ሠ. የዩኒቨርሲቲው ሬጅስትራር ፅሕፈት ቤት ኃላፊ፤

2. የኮሚሽኑ ፀሐፊ ከአባላት መካከል የሚመረጥ.

3. የኮሚሽኑ አባላት ከግማሽ በላይ አባላቱ ሲገኙ ምልአተ ጉባዔው ስለሚሞላ ስብሰባው ይካሄዳል.

## 9. የኮሌጅ ወይም የተቋም ወይም ፋክልቲ አስተባበሪ

1. የኤሌክትሮኒክ ትምህርት አስተባባሪ በኮሌጅ ወይም ተቋም ውይም ፋክልቲ ካሉ መምህራን መካከል በተቋሙ አሰራር መሰረት ይመረጣል፡፡
2. የኮሌጅ ኤሌክትሮኒክ ትምህርት አስተባባሪ ደረጃ በኮሌጅ ወይም ተቋም ውይም ፋክልቲ ካሉ የትምህርት ክፍል ኃላፊዎች ጋር ተመጣጣኝ ይሆናል፡፡
3. እንደ ኤሌክትሮኒክ ትምህርት ፕሮግራሞች ስፋትና ባህርይ በኮሌጁ ወይም ተቋም ውይም ፋክልቲ አካዳሚክ ኮሚሽን እየታየ ለየትምህርት ክፍሉ አስተባባሪ ሊመደብ ይችላል፡፡

## ክፍል ሶስት
## የተማሪዎች መብትና ግዴታ

## 10. የተማሪዎች መብት

በኤሌክትሮኒክ ትምህርት የሚሳተፉ ተማሪዎች የሚከተሉት መብቶች አሏቸው፡፡

1. በሚገባ የተዋቀሩ እና ተዛማጅ የሆኑ የትምህርት አይነቶች ፣ የማስተማሪያ ግብዓቶች ተሟልተውላቸው ጥራት ያለው ትምህርት የማግኘት፤

2. ሁሉም ተማሪዎች በመካከላቸው ያሉ እንደ የአስተዳደግ፣ የማንነት፣ የጤና፣ የችሎታ፣ የጾታ፣ በአካል ጉዳት እና የመሳሰሉትን ልዩነቶች ሳይገድባቸው እኩል የትምህርት ዕድሎችን የማግኘት፤
3. የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች የኤሌክትሮኒክ የትምህርት አይነቶችን፣ የቪዲዮዎች መግለጫ ፅሁፍ፣ አቻ የምልክት ቋንቋ ትርጉም፣ የስክሪን አንባቢ እና ተስማሚ የትምህርት አይነት ይዘት ያላቸው አማራጭ ፎርማቶችን እና አገልግሎቶችን የማግኘት፤
4. በመስመር ላይ የመማሪያ አካባቢዎች ውስጥ የተማሪ መረጃዎችን የግል መረጃቸው እና ደህንነታቸው እንዲጠበቅ፣
5. የአካዳሚክ ታማኝነት በሚረጋገጥበት እና እንደ ማጭበርበር እና ክህደት ያሉ ጥሰቶች በማይኖሩበት የትምህርት አካባቢ የመሳተፍ፤
6. ከትምህርት አይነት የሚጠበቁትን፣ ምደባዎችን፣ የውጤት አሰጣጥ መስፈርቶችን እና በትምህርት አይነት መርሃ ግብሮች ላይ ያሉ ማናቸውንም ለውጦችን በተመለከተ ከአስተማሪዎችና ከተቋሙ ጋር ግልጽ እና ወቅታዊ ግንኙነት የማድረግ፤
7. መሻሻል ያለባቸውን ጉዳዮች በመረዳት ወቅታዊ እና ገንቢ አስተያየት የማግኘት፤
8. ፍትሃዊ እና ግልጽ በሆነ መንገድ ውጤት የማግኘት እና የውጤት መመዘኛዎች ላይ በግልፅ የመነጋገር እንዲሁም ስህተት ተፈጥሯል ብለው ካመኑ በተቋሙ የአሰራር ስርዓት መሰረት የፈተና ወይም የምዘና ግምገማው በድጋሚ እንዲፈተሸ የመጠየቅ፤
9. የትምህርት እና የግል ፍላጎቶቻቸውን ለማሟላት የአካዳሚክ ምክር እና የቴክኒክ ድጋፍ አገልግሎቶችን የማግኘት፤
10. ስለ መስመር ላይ ትምህርት አይነት ተሳትፎ፣ የትምህርት አይነት መስፈርቶችን እና ጥቅም ላይ የዋለውን ቴክኖሎጂን ጨምሮ መረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ የማግኘት፤
11. በትምህርት ተቋማት ተገቢ ካልሆኑ ድርጊቶች የመከልከል እና ከተጋነነ ክፍያ ወይም ከአሳሳች ማስታወቂያዎች የመጠበቅ፤
12. የኤሌክትሮኒክ ትምህርት ውጤታማነት አስፈላጊ የሆኑ የቴክኒካል ስልጠናዎች እና ሌሎች ድጋፎች የማግኘት መብቶች አሏቸው።

## 11. የተማሪዎች ግዴታ

በኤሌክትሮኒክ ትምህርት የሚሳተፉ ተማሪዎች የሚከተሉት ግዴታዎች አሉባቸው፡፡

1. በውይይቶች ላይ በመሳተፍ እና ስራዎችን በሰዓቱ የማጠናቀቅ፤
2. ለትምህርት አይነቱ የተዘጋጀውን መርሃ ግብር ጠብቀው ትምህርታቸውን የመከታተል፤
3. ተማሪው በራሱ ተነሳሽነት የመማር ልምዱን ከመደበኛ የትምህርት አሰጣጥ እኩል ትኩረት የመስጠት፤
4. የኤሌክትሮኒክ ትምህርት የትምህርት አይነቶች ላይ ለመሳተፍ አስፈላጊውን ቴክኖሎጂ በማሟላት እና በመረዳት ለመጠቀም ዝግጁ የመሆን፤
5. እንደ አስፈላጊነቱ ከኤሌክትሮኒክ ትምህርት ጋር በተገናኘ ከአስተማሪዎችና ከክፍል ጓደኞች ጋር በመገናኘት በሚደረገው ውይይት ላይ የመሳተፍ፤
6. የተቋሙን ፖሊሲዎች፣ ህግና ደንቦችን የማክበር፤
7. የመስመር ላይ የትምህርት አይነት መስጫ የመማሪያ መፃህፍትን፣ ተጨማሪ ንባቦችን እና ዲጂታል ቤተ-መፃህፍትን በአግባቡ የመጠቀም፤
8. በሁሉም ኤሌክትሮኒክ ትምህርት መስተጋብር ውስጥ ከፍተኛ የሙያ ደረጃን ለመጠበቅ በውይይቶች፣ በኢሜይሎች ግንኙነቶች እና በመረጃ ልውውጦች ተገቢውን ቋንቋ፣ ሙያዊ የአገላለጽ ቃና እና ስነ-ምግባር የተላበሰ አነጋገርን የመጠቀም፤
9. የቡድን ስራ የትምህርት አይነቱ አካል ከሆነ በትብብር ስራዎች ላይ በንቃት የመሳተፍ እና ለቡድን ፕሮጀክቶች ድርሻን የማበርከት፤
10. በኤሌክትሮኒክ ትምህርት አሰጣጥ፣ በጥናት ልምድ እና በሚጠበቁ ስራዎች ላይ ማስተካከያ ሊፈልግ እንደሚችል በመገንዘብ ተለዋዋጭነትን የመቀበል።

## ክፍል አራት

## የማበረታቻ ስርዓት

### 12. በኤሌክትሮኒክ ትምህርት አሰጣጥ ስርዓት ለሚሰለጥኑና ለሚያሰለጥኑ መምህራን የሚደረግ ማበረታቻ

በኤሌክትሮኒክ ትምህርት አሰጣጥ ሥርዓት ውስጥ ለተሳተፉ አካላት እንደ ይዘት ዝግጅት ክብደት እና ባህርይ መሰረት የሚከተሉት ማበረታቻዎች ይደረጋሉ።

1. በኤልክትሮኒክ ትምህርት በትምህርት አይነት ዝግጅት እና በትምህርት አሰጣጥ ሂደት ላይ ተሳትፎ ላደረጉ መምህራን የምስክር ወረቀት በመስጠት፣ የሚሰጠውም የምስክር ወረቀት ለአመታዊ የስራ አፈፃጸም ምዘና እንደ አንድ መስፈርት ያገለግላል፡፡
2. በኤልክትሮኒክ ትምህርት የትምህርት አይነት የሚያስተምሩ መምህራን ከመደበኛ የማስተማር ስራ ጫና ጋር ተመጣጣኝ ሆኖ ይቆጠራል፡፡

3. በትምህርት ሚኒስቴር እዉቅና የተሰጠዉ ከኤልክትሮኒክ ትምህርት ጋር ተያያዥ የሆነ ከ 3 ወር ያላነሰ የአጭር ጊዜ ሥልጠና የሚሰለጥኑ መምህራን እንደ ከፍተኛ ዲፕሎማ ፕሮግራም ሠልጣኞች ተቆጥሮ ተመሳሳይ ማበረታቻ የሚያገኝ ሲሆን 3 ሳምንት እና ከ3 ወር በታች ስልጠና የወሰዱ መምህራን 2 ክሬዲት ይደረግላቸዋል፡፡
4. በትምህርት ሚኒስቴር እውቅና የተሰጠው ከኤልክትሮኒክ ትምህርት ጋር ተያያዥነት ያለዉ ከ 3 ወር እስከ 4 ወር ስልጠና የሚሰጥ አሰልጣኝ መምህር በመንፈቀ ዓመት 6 ክሬዲት እንዲሁም ከ 3 ወር ካነሰ ለያንዳንዱ የስልጠና ፕሮግራም የ 2 ክሬዲት ተቀናሽ ይደረግለታል።
5. በትምህርት ሚኒስቴር እውቅና የተሰጠው በኤልክትሮኒክስ ትምህርት ንድፍ ስራ ለተሳተፈ ባለሙያ መምህር፣ የንድፍ ስራ የሚሰራለትን የትምህርት አይነት ክሬዲት ግማሽ ለአንድ ሲሚስተር ብቻ ስራ ጫና ይያዝለታል፡፡
6. የኤልክትሮኒክስ ትምህርት ይዘትን ለሚያዘጋጅ መምህር አግባብነት ባለው በገንዘብ ሚኒስቴር መመሪያ መሰረት ማበረታቻውን እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡
7. የኤልክትሮኒክ ትምህርት ይዘት ከተዘጋጀበት ተቋም ውጪ ለሌላ ተቋም በገንዘብ የሚተላለፍ ከሆነ ይዘቱን ያዘጋጁት መምህራን ክፍያን በተመለከተ አግባብ ባለው ህግ መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል አምስት
## የመምህራን ግዴታዎች

### 13. ስልጠና መዉሰድ፣ ይዘት የማዘጋጀትና የትምህርት አይነት መስጠት

1. በትምህርት ሚኒስቴር እውቅና የተሰጠውን ከኤልክትሮኒክ ትምህርት ጋር ተያያዥነት ያለዉ ስልጠና ቀጣይነት ያለዉ የመምህራን የሙያ ማሻሻያ ፕሮግራም ሆኖ ለሁሉም መምህራን ይሰጣል።
2. የኤልክትሮኒክስ ትምህርት ይዘትን የሚያዘጋጅ መምህር በትምህርት ሚኒስቴር እውቅና የተሰጠውን ከኤልክትሮኒክ ትምህርት ጋር ተያያዥነት ያለዉን ስልጠና የወሰደ መሆን ይኖርበታል።
3. በኤልክትሮኒክስ ትምህርት አሰጣጥ ዘዴ የትምህርት አይነት የሚያስተምር መምህር በትምህርት ሚኒስቴር እውቅና የተሰጠውን ከኤልክትሮኒክ ትምህርት ጋር ተያያዥነት ያለዉን ስልጠና የወሰደ መሆን አለበት።

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**14. መመሪያውን ስለማሻሻል**

ይህ መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በትምህርት ሚኒስትሩ ሊሻሻል ይችላል፡፡

**15. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው መመሪያዎችና ልማዳዊ አሠራሮች**

በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ጋር የሚቃረኑ መመሪያዎች፣ ሰርኩላሮችና የአሰራር ሥርዓቶች ተፈጻሚነት አይኖራቸውም።

**16. መመሪያው ተፈጻሚ የሚሆንበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ተፈጻሚ የሚሆነው በፍትህ ሚኒስቴር ሕግ ተመዝግቦ፣ በትምህርት ሚኒስትሩ ከተፈረበት እና በፌዴራል ትምህርት ሚኒስቴር ድረ- ገጽ ላይ ከተጫነበት ዕለት ጀምሮ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ

ብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር)

የትምህርት ሚኒስትር